በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ስርዓት አፈጻጸም ውጤታማነት በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2011

አዲስ አበባ

ማውጫ

ማውጫ i

Executive summery i

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የድርጅቱ ራዕይ 1

የድርጅቱ ተልዕኮ 1

የድርጅቱ አላማ 2

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓት ልማት ድርጅት መዋቅርና 3

የሰው ኃይል ድርጅታዊ መዋቅር 3

የሰው ኃይል 3

የፋይናንስ ምንጭ 4

የኦዲቱ አላማ 4

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 4

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው አካባቢ 5

የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫ 5

የመመዘኛ መስፈርት 6

የአሰራር ስርዓት መግለጫ /Process description/ 7

ክፍል ሁለት 9

የኦዲት ግኝቶች 9

የኢንዱስትሪዎች ምርታማነትና ውጤታማነትን ለማሳደግ ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በጥራት፣ በብዛት እና በጊዜ ለኢንዱስ ትሪዎች የሚቀርብበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ 9

ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን ምርት በማምረት የሚያቀርብ ስለመሆኑ፣ 9

ድርጅቱ ግብዓቶችን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር 11

በግዢ የሚያቀርብ መሆኑን በተመለከተ 11

ድርጅቱ በእስትራቴጂክ ዓመታዊ ዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ 12

ማድረጉን በተመለከተ፣ መሆኑ በተመለከተ፣ 12

ድርጅቱ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖችና ተገቢ 14

የመገልገያ መሳሪያዎች የተደራጀ መሆኑን በተመለከ 14
ፋብሪካዎች በገቡት ውል የወሰዱትን ብድር እንዲመልሱ ማድረጉን እናበማይመልሱት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረጉን በተመለከተ 21
ድርጅቱ ግብዓቶች በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ 26
ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ 26
2. ድርጅቱ ኢንዱስትሪዎች በመደገፍ ውጤታማ እንዲሆኑ የምርት ግብዓት አቅርቦት ሰንሰለት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ 28
ድርጅቱ የገበያ ትስስር ሰንሰለት በመዘርጋ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣ 28
ድርጅቱ የብድር አሰጣጥ ውል በጥናት የተደገፈ መሆኑን በተመለከተ፣ 29
ድርጅቱ ውጤታማ ለሆኑ አቅራቢዎች የሚያበረታታ መሆኑ በተመለከተ፣ 30
ክፍል ሦስት 32
የመደምደሚያ ሀሳቦች 32
ክፍል አራት 32
የማሻሻያ ሀሳቦች 32
አባሪ 1 መመዘኛ መስፈርት i

Executive summery

1. የኦዲቱ አላማ ድርጅቱ የኢንዲስትሪ ግብዓቶች አቅርቦት ስርዓት በተመለከተ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በመገምገም አፈፃፀሙ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

2. ድርጅቱ የግብዓት አቅርቦቶችን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድርጅቶችን መገንባት ማስተዳደር አስፈላጊ ሲሆን ማስተላለፍ እንዲሁም ግብዓቶችን በአገር ውስጥና በውጭ አገር የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በማምረት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

3. ይሁን እንጂ ድርጅቱ የግብዓት አቅርቦት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድርጅቶችን መገንባት በተመለከተ ለምሳሌ የኢንዱስትሪውን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል ጥናት በማጥናት ችግሮችን በመለየት እና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ቅደም ተከተል (Priority) በማድረግ ውጤታማ በሆነ መልኩ የተሰራ ስራ አለመኖሩ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በማምረት ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ማቅረብ በተመለከተ የተሰራ ስራ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

4. ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን አስፈላጊውን ጥናት በማከናወን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ በመግዛት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

5. ይሁን እንጂ ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከአገር ውስጥ እና ከውጭ አገር በግዢ የሚያቀርብ ቢሆንም በጥናት የተደገፈና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ አለመሆኑታውቋል፡፡

6. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በዓይነት፣ በጥራት እና በብዛት በመለየት በእስትራቴጂክ ዕቅዱና በዓመታዊ ዕቅዱ በማካተት በዕቅዱ

መሰረት ተግባራዊ ያደረገና በክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች ላይ የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

7. ድርጅቱ የሚመራበት የረጅም ጊዜና የአጭር ጊዜ አቅጣጫ አመለካች የፀደቀ እስትራቴጂክ/ ዕቅድ የሌለው መሆኑ፣ ነገር ግን አመታዊ ዕቅድ ብቻ ያለው መሆኑ ታውቋል፡፡

8. ድርጅቱ ግብዓቶች ከጉዳት ተጠብቀው እንዲከማቹ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖችና ተገቢ የመገልገያ መሳሪያዎች እንደ ግብዓቱ ዓይነት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

9. ይሁን እንጂ ድርጅቱ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖች በማዘጋጀት እንደ ግብዓቱ ዓይነት በመለየት አስፈላጊ የሆኑ መገልገያ መሳሪያዎችና የመጋዘን መርጃ መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያልተደራጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

10. ድርጅቱ በዱቤ ሽያጭ ግብዓት ለሚረከቡ ኢንዱስትሪዎች ዋስትና እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

11. ድርጅቱ በዱቤ ሽያጭ ግብዓት የሚወስዱ ኢንዱስትሪዎች ለሚረከቡት ግብዓት ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና ወጥነት ባለው መልኩ እንዲያቀርቡ አልተደረገም፡፡

12. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ የሚያቀርባቸውን የተለየያዩ ግብዓቶች በገቡት ውል መሰረት በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ ተገቢውን ክትትል ሊያደርግና በወቅቱ በማይመልሱት ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

13. ይሁን እንጂ ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ የሚያቀርባቸውን የተለያዩ ግብዓቶች ውል እንዲፈጽሙ እና በገቡት ውል መሰረት በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ ተገቢውን ክትትል በወቅቱ ውጤታማ በሆነ መልኩ አለመደረጉ እንዲሁም በተቀመጠው ጊዜ በማይመልሱት ላይ ተገቢ እርምጃ በወቅቱ የማይወሰድ ሁኔታ መኖሩ ታውቋል፡፡

14. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ሊደግፍ ይገባል፡፡

15. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ኢንዱስትሪውን በሚፈለገው መልኩ እየደገፈ አይደለም፡፡

16. ድርጅቱ ቀልጣፋና ውጤታማ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የአቅርቦት ሰንሰለት ማኔጅመንት ሊተገብር ይገባል፡፡

17. ይሁን እንጂ ድርጅቱ የኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ በማቋቋሚያ ደንቡ ላይ የተገለጸ ቢሆንም ነገር ግን ድርጅቱ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የሆነ የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ሰንሰለት በመዘርጋ ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ አለመደረጉ ታወቋል፡፡

18. ድርጅቱ ከፋብሪካዎች ጋር የግብዓት የአቅርቦት ውል ከመፈጸሙ በፊት የፋብሪካዎቹ የቀደመ የፋይናንስ አቋም እና እዳ አከፋፈል ተገቢውን ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡

19. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ ግብዓት በሚያቀርብበት ጊዜ ዱቤ ከመስጠቱ በፊት የፋብሪካዎቹን አቋምና የዕዳ አከፋፈል በተመለከተ ተገቢውን ጥናት ሳያደርግ የዱቤ ሽያጭ የሚያደርግበት ሁኔታ መኖሩ ለማቅ ተችለዋል፡፡

20. ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በማቅረብ ውጤታማ ለሆኑ አቅራቢዎች ማበረታቻ የሚሰጥበትን ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

21. ድርጅቱ ኢንዱስትሪዎች ውጤታማና ቀጣይነት ያለው ግብዓት እንዲያገኙ ግብዓቶችን በማቅረብ ውጤታማ የሆኑ አቅራቢዎች ለማበረታት የሚያስችል ማበረታቻ የሚሰጥበት ስርዓት የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. በሀገሪቱ የኢንዱስትሪ መር የኢኮኖሚ ስርዓት ለመገንባት በተደረጉ ጥረቶች የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ዋና ችግር የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በተፈለገው ጥራት፣ መጠንና ጊዜ አለማግኘት ነው፡፡ ለግብዓት አቅርቦት ማነስ አይነተኛው ምክንያት የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት በሀገር ውሰጥ ማረጋገጥ ባለመቻሉና በአማራጭነት ከውጭ በጅምላ አስመጥቶ ለኢንዱስትሪዎቹ ማቅረብ የሚችል ድርጅት አለመኖሩ ነው፡፡ መንግስት ከፍተኛ እጥረት የሚታይባቸው እንደ ጥጥ፣ ቆዳ፣ ስንዴ ብቅልና ሌሎች የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በተለያዩ ድርጅቶችና አካላት በኩል በማስመጣት የግብዕት አቀርቦት ክፍተት ለመሙላት ጥረት ቢደረጉም ቀጣይነትና አስተማማኝ የግብዓት አቅርቦት ችግር መፍትሄ ማምጣት አልተቻለም፡፡
2. መንግስትም የቅድሚያ የትኩረት መስክ ከሰጣቸው ዘርፎች መካከል ለጨርቃ ጨርቅ፣ ቆዳ፣ አግሮ ፕሮሰሲንግ፣ እና ሌሎች የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በስፋት የሚያቀርብና ኤክስፖርት የሚያደርግ የመንግስት የልማት ድርጅት በማስፈለጉ በደንብ ቁጥር 328/2006 የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ ድርጅቱ በመንግስት የልማት ድርጅቶች በአዋጅ ቁጥር 25/1984 መሰረት ይተዳደራል፡፡

የድርጅቱ ራዕይ

3. በ2017 ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ግብዓት አቅርቦት ትስስር ውጤታማነት በማድረግ በአፍሪካ ተመራጭ ሆኖ መገኘት፣

የድርጅቱ ተልዕኮ

4. ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ የግብዓትና የኢንዱስትሪ ውጤቶችን ገዝቶ በማቅረብ፣ ፕሮጀክቶች በማልማት፣ በማስተዳደርና በማስተላለፍ በሰው ሀብትና በቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርዓቶችን በመተግበር ተወዳዳሪና ውጤታማ ኢንዱስትሪዎች እንዲፈጠሩ ማገዝ ነው፡፡

የድርጅቱ አላማ

5. ድርጅቱ በደንብ ቁጥር 328/2006 መሰረት የሚከተሉት አላማዎች አሉት፣

- የኢንዱስትሪ ግብዓቶች አቅርቦት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድርጅቶችን መገንባት፤ ማስተዳደር አስፈላጊ ሲሆን ማስተላለፍ፡፡
- በአገር ውስጥና እና በውጭ አገር የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በማምረት ማቅረብ፤
- የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በመግዛት ማቅረብ፤
- ከአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ፍጆታ በላይ የሆኑትን የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ወደ ውጭ አገር መላክ፤
- የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት እና ጥሬ ዕቃ በማቅረብ ከተሰማሩ ድርጅቶች ጋር በጋራ መስራት፣
- ቀልጣፋና ውጤታማ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የአቅርቦት ሰንሰለት ማኔጅመንት መተግበር፤
- ተመሳሳይ አላማ ካላቸው በአገር ውስጥና በውጭ አገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ፤
- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያ እና ፖሊሲ አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና የማስያዝና እና ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤
- አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ስራዎች ማከናወንና
  - እንዲሁም የሸቀጦች ጅምላ ንግድ ድርጅት (ጅንአድ) የተመለከቱ ተግባራትን ያከናውናል፡፡ እነርሱም፡-
- ሸቀጦችን ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር መግዛትና በጅምላ መሸጥ ሌሎችም ማስመጣት

- መሰረዊ ሸቀጦችን ከሀገር ውጥ እና ከውጭ አገር እየገዛ በመሸጥ ገበያ ማረጋጋት፣
- ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር አምራቾችና አቅራቢዎች የአደራ እና የውክልና ሽያጭ ስራዎችን ማካሄድ፣
- የድርጅቱን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ስራዎችን ማከናወን ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓት ልማት ድርጅት መዋቅርና

የሰው ኃይል ድርጅታዊ መዋቅር

6. የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት በዋና ስራ አስፈጻሚ የሚመራ ሲሆን ዋና ስራ አስፈጻሚውና የውስጥ ኢዲት ለድርጅቱ የስራ አመራር ቦርድ ተጠሪ ሲሆን ድርጅቱ ተጠሪነቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሆኖ እንዲዋቀር ተደርጓል፡፡ የድርጅቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ በስሩ አራት ምክትል ስራ አስፈጻሚዎች ማለትም የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ጥናት ትግበራና ልማት ዘርፍ ም/ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ የግዢ ዘርፍ ም/ዋና ስራ አስፈጻሚ ፣ የሽያጭ ዘርፍ ም/ዋና ስራ አስፈጻሚ እና የኮርፖሬት ሰርቪስ ዘርፍ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ ሲሆኑ እንዲሁም በቀጥታ ለዋና ስራ አስፈጻሚው ስድስት ዳይሬክቶሬቶች ተጠሪ ሆነው እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡

የሰው ኃይል

7. የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት ዋና መ/ቤትና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አደረጃጀትና መዋቅር መሰረት የተፈቀደ አጠቃላይ 457 እንደ አስፈላጊነቱ የሚጨምር ሲሆን እሰከ የካቲት 2011 ድረስ የተሸፈነ የስራ መደብ 1541 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 1501 ቋሚ እና 40 የኮንትራት ሰራተኛ ናቸው፡፡ የቋሚ ሰራተኞች ፕሮፋል በትምህርት ደረጃ ሲታይ ማስተርስና ከዚያ በላይ 15 በመጀመሪያ ዲግሪ 192 በዲፕሎማ 292 እንዲሁም ከዲፕሎማ በታች 1002 ናቸው፡፡

የፋይናንስ ምንጭ

8. የድርጅቱ የመንግስ የልማት ድርጅት ሲሆን የገንዘብ ምንጭ በራሱ በሚያገኘው ሲሆን ገንዘቡ የሚመደበው ለደመወዝ ለስራ ማስኬጃ እና ለካፒታል ሲሆን በ2008፣ በ2009 እና በ2010 በጀት አመታት ለሚያከናውናቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ እንደቅደም ተከተላቸው መደበኛ በጀት ብር 9,853,910.000,፣ ብር 8,733,923.000፣ እና ብር 3,374,133.000 በድምሩ ብር 21,961,966.000 ሲሆን ለሚተገብራቸው ተግባራት ማስፈጸሚያ ከተመደበው በጀት ውስጥ እንደ ቅደም ተከተሉ ብር 6,183,867.000፣ ብር 3,954,322.000፣ እና እስከ ታህሳስ 30 2010 ድረስ ብር 905,929.000 በድምሩ ብር 11044118.000 በስራ ላይ አውሏል፡፡

የኦዲቱ አላማ

9. የኦዲቱ አላማ ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች አቅርቦት ስርዓት በተመለከተ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መደረጉን በመገምገም አፈፃፀሙ ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ የአሰራር ችግሮች ካሉ ችግሮቹን በመለየት ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለማቅረብና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

10. ኦዲቱ በኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓት አቅራቢ ልማት ድርጅት የተከናወነ ሲሆን ከጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ ከቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ ከባህርዳር ቆዳ ፋብሪካ፣ ከሀበሻ ታኒግ ቆዳ ፋብሪካ፣ ከኢትዮ ሌዘር ቆዳ ፋብሪካ፣ ከኢትዮጵያ ቆዳ ፋብሪካ ከሆራ ቆዳ ፋብሪካ ፣ ከኢትዮ ቆዳ ፋብሪካ ፣ ከአይካ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፕ፣ ከባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ አክስዮን ማህበር፣ ከኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ አክስዮን ማህበር፣ ከኤም ኤን ኤስ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ከኤስ ኤም ኤን ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ከአርባምንጭ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የስራ ኃላፊዎች ጋር በአካል ተገኝቶ ቃለ መጠይቅ በማድረግና ከድርጅቱ የስራ ኃላፊዎች ጋር የኦዲት ቡድኑ ቃለ መጠይቅ በማቅረብ

ከኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ጋር ተያያዥ ያላቸው ሰነዶች በመከለስ ማስረጃ ተሰብስቧል፡፡

11. ኦዲቱ የሸፈነው ሶስት የበጀት ዓመታትን ሲሆን ማለትም ከ2008 እስከ 2010ዓ.ም ባለው ጊዜ የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ስርዓትን በተመለከተ የተከናወኑ ስራዎችን ነው፡፡

ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው አካባቢ

12. ከላይ የተመለከቱትን የኦዲት ዘዴዎች በመጠቀም መረጃዎችና ማስረጃዎች መሰረት በማድረግ ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው አካባቢ የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ስርዓት አፈጻጸም ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫ

13. ከላይ የተገለጸውን የኦዲት አላማ ለማሳካት ሁለት ዋና የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች የተለዩ ሲሆን በሁለቱም የትኩረት አቅጣጫዎች ሥር ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡ እነርሱም

1. ድርጅቱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን በምርት ጥራት ተወዳዳሪ እንዲሆኑና እንዲጎለብቱ እንዲሁም ሀገሪቱ በዘርፉ የምታገኘውን ገቢ ለማሳደግ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የግብዓት አቅርቦት ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፣
    - 1.1 የኢንዱስትሪዎች ምርታማነትና ውጤታማነት ለማሳደግ ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በጥራትና በብዛት እና በጊዜ ለኢንዱስትሪዎች የሚቀርብበት የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣
    - 1.2 ድርጅቱ ኢንዱስትሪዎች በመደገፍ ውጤታማ እንዲሆኑ የምርት ግብዓት አቅርቦት ሰንሰለት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣
2. ድርጅቱ፣ ከየሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን አፈጻጸም ለማሳደግ እና ለመደገፍ በቅንጅት የሚሰሩበት አሰራር መኖሩን እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ ማደረጉን መገምገምየሚሉ ናቸው፡፡

የመመዘኛ መስፈርት

14. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን እና ሁለት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 15 የኦዲት የመመዘኛ መስፈርቶች(Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል

የአሰራር ስርዓት መግለጫ /Process description/

15. የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን አቅርቦት በሶስት የስራ ክፍሎች ይከናወናል፡፡ እነርሱም የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ም/ል ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ የግዢ ዘርፍ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ እና የሽያጭ ዘርፍ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ ናቸው፡፡
16. የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ም/ል ዋና ስራ አስፈጻሚ፣ የዘርፉን የአጭር፣ የመካከለኛ የረጅም ጊዜ ስትራቴጂክ ዕቅዶች በማዘጋጀት በየስራ ክፍሎቹ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ በሚዘጋጀው እስትራቴጂክ ዕቅድ የገበያውን ሁኔታ ያገናዘበ እና የደንበኛ ፍላጎት ማርካት የሚያስችል መሆኑን ያረጋግጣል፣ የገበያ ዳሰሳ ጥናቶች በማከናወን ወቅታዊ የሆኑ የገበያ ፍላጎቶች መረጃዎችን ያሰባስባል፣ የተጠቃሚ እርካታዎችን በመዳሰስና ተንትኖ በማቅረብ በመረጃ መረብ አማካኝነት ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሙሉ እንዲደርስ ያደርጋል፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የአቅርቦት ሰንሰለት ማኔጅመንት ይተገብራል፣ የኢንዱስተሪ ግብዓቶች ከቅድመ ምርት ዝግጅት ጀምሮ ለግብዓትነት እስከሚቀርብ ጊዜ ድረስ ባለው ሂደት ምርታማነትን እና ጥራቱን ጠብቆ ለኢንዱስትሪ የሚቀርብበትን እና አምራቹን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ አሰራር እንዲዘረጋ በማድረግ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡
17. የግዢ ዘርፍ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ግዢን አስመልክቶ የረጅም፣ መካከለኛና የአጭር ጊዜ አስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት ያቀርባል፣ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ አገር በመግዛት ያቀርባል፤ በአገር ውስጥና በውጭ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በማምረት ያቀርባል፤ በየበጀት ዓመቱ የሚከናወኑ የግዢዎችን በዓይነትና በመጠን በመለየት የግዢ ፕሮግራም በማውጣት አፈጻጸሙን ይከታተላል ይቆጣጠራል፤ ከፍተኛ ግዢዎች በጨረታ ወይም በቀጥታ ግዢ ከሀገር ውስጥ ሆነ ከውጭ አገር እንዲገዙ ሲወሰን አስፈላጊ ሰነዶች የግዢ ፎርማሊቲዎች መሟላታቸው በማረጋገጥ፣ በደንብና መመሪያ መሰረት ግዢ እንዲፈጸም ያደርጋል፣ ተገዝተው ወደ ድርጅቱ መጋዘን የመጡ ዕቃዎች ጥራት፣ ብዛት መጠን በማረጋገጥ ርክክብ መፈጸሙንና አስፈላጊ ምዝገባ መከናወኑንና በተገቢው መንገድ መከማቸቱን ያረጋግጣል ይቆጣጠራል፣

18. የሽያጭ ዘርፍ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ የየዘርፉን አጭር፣ መካከለኛ የረጅም ጊዜ ስትራቴጂ ዕቅዶችን በማዘጋጀት በስራ ክፍሎቹ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የሽያጭና የክምችት መመሪያ በማዘጋጀት ስራ ላይ ያውላል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣ የድርጅቱን የግብዓት ሽያጭ፣ ክምችትና ማከፋፈል ስራዎች የስራ ፕሮግራም እንዲዘጋጅ ያደርጋል አፈጻጸሙን በመገምገም ሪፖርት ያደርጋል፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲት ግኝቶች

የኢንዱስትሪዎች ምርታማነትና ውጤታማነትን ለማሳደግ ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በጥራት፣ በብዛት እና በጊዜ ለኢንዱስ ትሪዎች የሚቀርብበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋቱና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን ምርት በማምረት የሚያቀርብ ስለመሆኑ፣

19. ድርጅቱ የግብዓት አቅርቦቶችን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድርጅቶችን መገንባት ማስተዳደር አስፈላጊ ሲሆን ማስተላለፍ እንዲሁም ግብዓቶችን በአገር ውስጥና በውጭ አገር የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በማምረት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

20. ይሁን እንጂ በድርጅቱ ቀርበው በተከለሱ ማስረጃዎች እንደታየው ድርጅቱ የግብዓት አቅርቦት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድርጅቶችን መገንባት ማስተዳደር እንዲሁም አሰፈላጊ ሲሆን ማስተላለፍ፣ እንዳለበት በመቋቋሚያ ደንቡ 328/2006 የተቀመጠ ቢሆንም ነገር ግን በድርጅቱ ይህን በተመለከተ ለምሳሌ የኢንዱስትሪውን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል ጥናት በማጥናት ችግሮችን በመለየት እና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ቅደም ተከተል (Priority) በማድረግ ውጤታማ በሆነ መልኩ የተሰራ ስራ አለመኖሩ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በማምረት ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ማቅረብ ያለበት ቢሆንም ይህን በተመለከተ የተሰራ ስራ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

21. በድርጅቱ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅና በሰጡት መልስ የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት /ኢ.ኢ.ግ.ል.ድ/ በሚንስትሮች ም/ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 328/2006 በታህሳስ 2006 ዓ.ም. የተቋቋመ ቢሆንም ሥራ የጀመረው በዓመቱ በሰኔ ወር 2007 ዓ.ም. ነው፡፡ በ2007 በጀት ዓመት ጊዜያዊ የተዳመጠ ጥጥ ግዢና ሽያጭ መመሪያ በቦርድ በማፅደቅ የተዳመጠ ጥጥ ከአገር ውስጥ እና ከውጪ አገር ገዝቶ በማስገባት ለጨርቃ

ጨርቅ ኢንዱስትሪዎቹ ያቀረበ ሲሆን ድርጅቱ በተጓዳኝ የመሰረታዊ ሸቀጦች የማሰራጨቱን ሥራ ጐን ለጐን እየሰራ ቀጥሏል፡፡ እንዲሁም ድርጅቱ የተቋመበትን አላማ በተገቢው ለማስፈፀም እንዲያስችለው በአዲስ መልክ ድርጅታዊ መዋቅርና የደመወዝ ስኬል ማስጠናት ስለነበረበት ይህ ተግባር እስከ 2008 ዓ.ም. ድረስ ጊዜ የወሰደ መሆኑ፣ ከዚህ በተጨማሪ በማቋቋሚያ ደንቡ ላይ በጥሬ ገንዘብ መከፈል ከነበረበት ውስጥ ብር 792 ሚሊየን ብር ያልተከፈለ በመሆኑ በዚህ የተነሳ በማቋቋሚያ አዋጅ ላይ የተመለከተውን ግብዓት አምራች ኢንዱስትሪ ማቋቋም ያልተቻለ መሆኑ፣ በሌላ በኩል በፎርክሌዥር ሂደት ላይ የሚገኘውን የመርሳ ቆዳ ፋብሪካን ለመግዛት የአዋጭነት ጥናት አጥንቶ ለውሳኔ ለሚመለከተው የበላይ አካል ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ያቀረበ ቢሆንም ጥናቱ ተቀባይነት ስላላገኘ ወደ ሥራ ያልተገባ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

22. የድርጅቱ የሥራ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ድርጅቱ የራሱ የሆነ የቆዳ ፋብሪካ እንዲኖረው የመርሳ ቆዳ ፋብሪካን ግዢ ለማከናወን የአዋጭነት ጥናት አጥንቶ ለሚመለከተው አካል ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የቀረበ እንደሆነ ቢገልጹም የተላከበት ማስረጃ እና ምላሽ የተሰጠበት ማስረጃ በኦዲቱ ወቅት ያልቀረበ መሆኑ እንዲሁም የአዋጭነት ጥናቱ ለቦርድ ቀርቦ በወቅቱ ቦርዱ ገምግሞ የአዋጭነት ጥናቱ እንደገና በተጠናከረ መልኩ ተጠንቶ እንዲቀርብ በ22/04/09 ዓ.ም አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በድርጅቱ ከልሶ እንደገና ያቀረበ ስለመሆኑ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

23. በመሆኑም የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን አቅርቦት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድርጅቶች ተገንብተው ስራ እንዲወሉ ባለመደረጉ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በጥራት፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና በወቅቱ ለኢንዱስትሪዎች እንዳይደርሱና በማድረግ ለተቋቋመበት አላማ እንዳይሳካ ከማድረጉም በላይ ሀገሪቱ ከዘርፉ ለማግኘት የምታቅደውን ገቢ አፈጻጸም በግብዓት እጥረት ምክንያት እንዳይሳካ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

ድርጅቱ ግብዓቶችን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በግዢ የሚያቀርብ መሆኑን በተመለከተ

24. ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችንአስፈላጊውን ጥናት በማከናወን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ በመግዛት ሊያቀርብ ይገባል፡፡

25. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ በድርጅቱ ቀርበው በኦዲት ቡድኑ በተከለሱ ማስረጃዎች እንደታየው ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከአገር ውስጥ እና ከውጭ አገር በግዢ የሚያቀርብ ቢሆንም በጥናት የተደገፈና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

26. እንዲሁም የድርጅቱ በ2008 በጀት ዓመት የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ዘርፍ ያለውን የግብዓት ችግር ለመፍታት በብር 270 ሚሊዮን በግዢ ለማቅረብ አቅዶ ግዥው ያልተፈጸመ መሆኑ፣ በ2008 ዓ.ም የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ዘርፍ የሚፈለጉ ግብዓቶችን ማለትም የተዳመጠ ጥጥ፣ ብትን ጨርቅ፣ አክሰሰሪና ትሪም ቀለም እና ኬሚካሎችን በግዢ ለማቅረብ 1.9 ቢሊዮን ማለትም ብትን ጨርቅ 6 ቶን ዋጋው 2,250፣ አክሰሰሪና ትሪም 15 ቶን በዋጋ 1,017 እንዲሁም ቀለም 284 ቶን በዋጋ 127,800 ለማቅረብ ያቀደ ቢሆንም የተዳመጠ ጥጥ ግዢ ብቻ የተፈጸመ ሲሆን ሌላው ያልተከናወነ መሆኑ፣ እንዲሁም በምግብና በመጠጥ ፋርማሲውቲካል ኢንዱስትሪ ዘርፍ ያለውን የማሸጊያ ወረቀት ችግር ለመፍታት በ2008 ዓ.ም ብር 313.8 ሚሊዮን የማሸጊያ ወረቀት ግብዓት ግዢ ለመፈጸም ታቅዶ ግዢው አለመከናወኑ ታውቋል፡፡

27. በተጨማሪም በ2009 በጀት አመት የማኑፋክቸሪንግ ግብአቶች ግዢም ሆነ ሽያጭ አፈጻጸም ከ 50% በታች መሆኑ በ2010 በጀት ዓመት በመጠን 9199ቶን ጥጥ (1500ቶን ከውጭ) በዋጋ ብር 357.1 ሚሊዮን የተዳመጠ ጥጥ ለመግዛት ታቅዶ አፈጻጸሙ በመጠን 2538 ቶን በዋጋ ብር 95.8 ሚሊዮን ሲሆን ይህም ክንውኑ በመጠን 27.5% በመቶ እና በዋጋ 26.83% ዝቅተኛ መሆኑ ያሳያል፡፡

28. በድርጅቱ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በማቋቋሚ ደንቡ ላይ የተመለከተው በጥሬ ገንዘብ ሊከፈል የሚገባው 792 ሚሊዮን እንደሚከፈለው፣ ከውጭ አገርና ከአገር ውስጥ ለሚገዛ ጥጥ

በቀድሞው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተሰጠው የብድር ዋስትና እንደሚቀጥል /የብድር ዋስትና ማራዘሚያ ፈቃድ እንደሚገኝ/፤ ግብዓት በዱቤ የገዙ ኢንዱስትሪዎች በውሉ መሠረት የዱቤ እዳቸውን በዕዳ በመክፈያ ጊዜ ሰሌዳው መሠረት እንደሚከፍሉ፤ ለኬሚካል፣ ለብረታ ብረት፣ ለማሸጊያ ወረቀት… ወዘተ ለሚካሄደው የውጪ ግዥ የውጪ ምንዛሬ አቅርቦት እንደሚኖር፣ ብድርም እንደሚመቻች የዕቅድ ታሳቢ የተቀመጠ ሲሆን፤ በዚህ አግባብ ባለመሆኑ በእቅዱ መሠረት አለመከናወኑን ገልጸዋል፡፡

29. በተጨማሪም በረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት ምላሽ ድርጅቱ በየበጀት ዓመቱ ግብዓት ለማቅረብ ያቀደውን እንዳይፈጽም ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች ያገጠሙት መሆኑ ይህም በተለይ የአቅም ማነስ ፣ የቴክኒክ አቅም ውስንነት ኋላ ቀር የግዢ አሰራር ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ገልጸዋል፡፡

30. በመሆኑም ድርጅቱ ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በግዢ በሚፈለገው መልኩ የማያቀርብ በመሆኑ፣ ኢንዱስትሪው የሚያስፈልገውን ግብዓት ተጠቅሞ ጥራት ያለውና ተወዳዳሪ ምርት በማምረት በወቅቱ እንዳያቀርብና ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

ድርጅቱ በእስትራቴጂክ ዓመታዊ ዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣ መሆኑ በተመለከተ፣

31. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በዓይነት፣ በጥራት እና በብዛት በመለየት በእስትራቴጂክ ዕቅዱና በዓመታዊ ዕቅዱ በማካተት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ያደረገና በክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች ላይ የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

32. ጉዳዩን አስመልክቶ በድርጅቱ ቀርበው በኦዲት ቡድኑ በተከለሱ ማስረጃዎች እንደታየው ድርጅቱ የሚመራበት የረጅም ጊዜና የአጭር ጊዜ አቅጣጫ አመለካች የፀደቀ እስትራቴጂክ/ ዕቅድ የሌለው መሆኑ፣ ነገር ግን አመታዊ ዕቅድ ብቻ ያለው መሆኑ ታውቋል፡፡

33. ይሁን እንጂ በድርጅቱ በዓመታዊ ዕቅዱ መሰረት ስለመፈፀሙ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡-

- ድርጅቱ በ2008 በጀት አመት የቆዳ እና ሌጦ በብር 171.04 ሚሊዮን ለመሸጥ አቅዶ ነገር ግን በብር 18.1 ሚሊዮን ብቻ ያከናወነና አፈጻጸሙ ዝቅተኛ መሆኑ፣ በ2009 በጀት ዓመት የብር 4.4 ቢሊዮን ግብዓቶች ገዝቶ በብር 4.5 ቢሊዮን ለመሸጥ የታቀደ ቢሆንም ክንውኑ ብር 524 ሚሊዮን (12 በመቶ) ግዢ እና 394 ሚሊዮን አፈጻጸሙ (9 በመቶ) ሽያጭ ብቻ አከናውኗል፡፡
- በ2010 በጀት ዓመት በቆዳና ሌጦ ዘርፍ ብር 106 ሚሊዮን ዋጋ ያለው ጥሬ ቆዳና ሌጦ፣ ዌት ብሉ ያለቀለት ቆዳ በሽያጭ ለማቅረብ ታቅዶ ብር 16.7 ሚሊዮን መሆኑን አፈጻጸሙ 17% አነስተኛ መሆኑ፣ ጥሬ ቆዳና ሌጦ 51 ሚሊዮን ዋጋ ያለው ለፋብሪካዎች በሽያጭ ለማቅረብ ታቅዶ 10.5 ሚሊዮን ብር በቁጥር 164,300 የበግ ሌጦ እና 30,000 የፍየል ሌጦ የቀረበ ሲሆን አፈጻጸሙ ከዕቅዱ አንጻር 21 በመቶ መሆኑ፣ በከፊል የለፉ ቆዳ 42.7 ሚሊዮን በዋጋ ለማቅረብ ታቅዶ አፈጻጸሙ በብር 3.9 (18 በመቶ) መሆኑ፣ እንዲሁም ያለቀለት ቆዳ ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በብር11.5 ሚሊዮን ዋጋ ለማቅረብ ታቅዶ ብር 2.3 ሚሊዮን ዋጋ የተከናወነ ሲሆን አፈጻጸሙ 21 በመቶ ዝቅተኛ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- በ2010 በጀት ዓመት በመጠን 86,400 ቶን በዋጋ ብር 416.8 ሚሊዮን የሆነ የኢንዱስትሪ ጨው በሽያጭ ለማሰራጨት ታቅዶ ክንውኑ 11,065 ቶን በዋጋ ብር 52 ሚሊዮን ሲሆን አፈጻጸሙ በመጠን 13 በመቶ እና በዋጋ 12 በመቶ ዝቀተኛ ሲሆን
- በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ በብር 196 ሚሊዮን አግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ለመግዛት ታቅዶ ክንውኑ 85.7 በመሆኑ አፈጻጸሙ 44 በመቶ መሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

34. በተጨማሪም ድርጅቱ ለኢንዱስትሪው ግብዓት አቅርቦት አፈጻጸም ማነስ መንስኤ የሆኑ ዋና ዋና ማነቆዎች በመለየት ቀጣይ የሚፈቱበት አቅጣጫ ከማመላከት አኳያ ክፍተት መኖሩ ከተከለሱ ሰነዶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

35. በድርጅቱ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ድርጅቱ በወቅቱ ስትራቴጂክ እቅድ እና የኦፕሬሽን እቅድ አዘጋጅቶ

ለሥራ አመራር ቦርድ ያቀረበ ሲሆን የኦፕሬሽን እቅዱ ፀድቆ የስትራቴጂክ እቅዱ አልፀደቀም፡፡ እንዲሁም የሥራ አመራር ቦርድ መለዋወጥ እና ድርጅቱ ለተቋቋመበት ተልዕኮ አዲስ በመሆኑ የሌሎችን ልምድ ቀስሞ የስትራቴጂክ እቅድ እንዲዘጋጅ ከበላይ አመራር አቅጣጫ ስለተሰጠ የፀደቀ የስትራቴጂክ እቅድ አልነበረውም፡፡ በአሁኑ ሰዓት ድርጅቱ በ2011 በጀት ዓመት የሰባት ዓመት ስትራቴጅክ እቅድ አዘጋጅቶ በሠራተኞች፣ በህዝብ ክንፍና በባለድርሻ አካላት ተተችቶ እንዲፀድቅ ለሥራ አመራር ቦርድ የቀረበ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

36. በመሆኑም እስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት ዕቅዱን መሰረት አድርጎ ዓመታዊ ዕቅድ በማቀድ ተግባራዊ ባለመደረጉ ድርጅቱ በደንቡ ላይ የተቀመጠውን አላማ ለማሳካት ከየት ተነስቶ ወዴት ለመድረስ በሚያስችል መልኩ (road map) መሰረት እንዳይፈፅም በማድረግ በየጊዜው በአፈጻጸሙን ውጤታማ በሆነ መልኩ ስለማከናወኑ አስፈላጊውን ግምገማ በማድረግ ችግሮችን እንዳይቀርፍ ከማድረጉ በተጨማሪ የተቋቋመበትን አላማ ውጤታማ እና በብቃት እንዳይወጣ አድርጓል፡፡

ድርጅቱ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖችና ተገቢ

የመገልገያ መሳሪያዎች የተደራጀ መሆኑን በተመለከ

37. ድርጅቱ ግብዓቶች ከጉዳት ተጠብቀው እንዲከማቹ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖችና ተገቢ የመገልገያ መሳሪያዎች እንደ ግብዓቱ ዓይነት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡

38. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ በድርጅቱ ቀርበው በኦዲት ቡድኑ በተከለሱ ማስረጃዎች እንደታየው ድርጅቱ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖች በማዘጋጀት እንደ ግብዓቱ ዓይነት በመለየት አስፈላጊ የሆኑ መገልገያ መሳሪያዎችና የመጋዘን መርጃ መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያልተደራጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

39. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ለታዩ ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበው ቃለ መጠይቅ የሰጡት መልስ እንደሚከተለው ተቀምጧል፡፡

- ኤም ኤን.ኤስ ስለኤግልድ የግብዓት አያያዝን በተመለከተ ድርጅቱ የስቶር አያያዝ ችግር ያለበት መሆኑን እንዲሁም የሮር ክሊፍት ችግር መኖሩና መጋዘኖቹ መተላለፊያቸው በጣም ጠባብ በመሆናቸው እሳት ቢነሳ እንኳ

ለመከላከል አስቸጋሪ እንደሆነ፤ ከተለያዩ ቦታ የመጡ ምርቶች እንደ ጥራታቸው ደረጃ ተሰጥቶአቸው የተለያየ ቦታ ሊቀመጡ ሲገባ ተቀላቅለው የሚቀመጡና ለመለየት አስቸጋሪ እንደሆኑ፤ የጥጥ አቀማመጡም ወለል ላይ የሚቀመጥ በመሆኑ ቅዝቃዜ ስቦ የክብደትና የከለር ለውጥ በማምጣት የነበረውን ጥራት የሚቀንስ መሆኑን፣

- በኮምቦልቻ መልካዲስ መጋዘኖች የጥጥ መጫኛና ማውረጃ ፎርክሊፍት ባለመኖሩ የርክክብ ስርዓቱ ቀልጣፋ አለመሆኑ፣
- እንዲሁም የአይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፐም ድርጅቱ ስቶር ላይ ፎርክሊፍት የሌለና ፋብሪካው የራሱን በመላክ እንደሚጠቀምና ያም በመሆኑ በስራ ላይ መጓተት እንደፈጠረባቸውና ለተለያየ ወጪ የዳረጋቸው መሆኑ ገልጸዋል፡፡
- የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ መጋዘኑ የፎርክሊፍት ችግር ያለበትና ለመጫን ችግር መሆኑ፣ የስቶር ችግር ያለበትና እሳት ቢነሳ እንኳን መውጫ የሌለ መሆኑ፤ ማስቀመጫ የሌለና መሬት ላይ የሚቀመጥ መሆኑ አስረድተዋል፡፡

(በቃሊቲ የጥጥ መጋዘን የጥጡ ጥራት በሚጠበቅበት ሁኔታ ያለልተቀመጠ መሆኑን የሚያሳይ ፎቶ ቁ.1)

40. እንዲሁም የኦዲት ቡድኑ በናሙና በተመረጡ መጋዘን ተገኝቶ ምልከታ ባደረገበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

- በቃሊቲ በጥጥ መጋዘን ውስጥ የጥጡ ለአቀማመጥ መሬት ላይ ያለማስቀመጫ የሚቀመጥ በመሆኑ ከስር ያለ ጥጥ በእርጥበት የሚበላሽበት ሁኔታ መኖሩ፣
- እንዲሁም ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ቃሊታ መጋዘን የገባ አርማታ ብረት ባለ 18 ዴክሬን 2004 ኪ.ግ፣ ባለ 12 አቢስኒያ 95.904.ኪ.ግ፣ በለ 10 1,362,683.988 ኪ.ግ ፣ባለ 26 2086 ኪ.ግ፣ ባለ 28 522.90 ኪ.ግ፣ ባለ 30 199.83 ኪ.ግ ዴክሬን በአጠቃላይ 1,367,592.622 ኪ.ግ የአርማታ ብረት በግቢ ውስጥ ለዝናብና ለጸሀይና ለአቧራ ተጋልጠ የሚገኝና ለብክነት እየተዳረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

(*በቃሊቲ የውጪ የብረት መጋዘን ብረት በሚባክንበትና ደህነቱ በሚጠበቅበት ሁኔታ ያልተቀመጠ መሆኑን የሚያሳይ ፎቶ ቁ.2)*

41. እንዲሁም በቃሊቲ የመጋዘን ቁጥጥርና አስተዳደር ደካማ በመሆኑ እና እቃ ሲገባና ሲወጣ ተገቢ የሆነ ክትትል ባለመደረጉ በቃሊቲ መጋዘን የገቢ ሰነድ ሳይቆረጥለት የአርማታ ብረት በብልጫ የብር 1,764,617.92 (የአንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ስልሳ አራት ሺህ ስድስት መቶ አስራ ሰባት ብር ከ 92/100 ሳንቲም) የአርማታ ብረት በቆጠራ ወቅት መገኘቱ፣ በተጨማሪም ብር 908,434.63 (ዘጠኝ መቶ ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰላሳ አራት ብር ከ63/100 ሳንቲም የአርማታ ብረት በክምችት ከተመዘገበው በላይ ተሸጦ የተገኘ መሆኑ፤

42. በተጨማሪም ከጁላይ 7 2015 እስከ ማርች 3,2018 ድረስ የአርማታ ብረት የተጨማሪ እሴት ታክስ ጨምሮ 33,386,174.36 ብር (ሰላሳ ሶስት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሰባ አራት ከ36/100 ሳንቲም ጉድለት መታየቱን ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

43. በድርጅቱ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የመጋዘን መርጃ መሣሪያዎች (እንደፎርክሊፍት) ያሉት

እንደሚያስፈልጉ ግልፅ መሆኑ፣ ለተዳመጠ ጥጥ እና ለብረታ ብረት ግብዓት ከተመረጡት መጋዘኖች ዋነኛውና ትልቁ የድርጅቱ ቃሊቲ ሽያጭ ቅርንጫፍ ሲሆን በዚህ ቅርንጫፍ ሦስቱ ፎርክሊፍቶች አገልግሎት እየሰጡ እንደሆኑ ኮምቦልቻ፣ ሲድሃፋጌ/መልካሰድ/ እና ጉንደር ሽያጭ ቅርንጫፎች ላሉ መጋዘኖች ፎርክሊፍቶች ለመግዛት ላለፉት ሦስት ዓመታት በጀት ተይዞ ጨረታ ተጫርቶ አሸናፊው ተለይቶ በውጪ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ግዥ መፈፀም ያልተቻ መሆኑ ነገር ግን ችግሩን ለመቅረፍ የሦስተኛ ወገን ፎርክሊፍቶችን በኪራይ የሚጠቀሙ እንደሆነ በተጨማሪም በ2011 በጀት ዓመትም 5 ፎርክሊፍቶች ለመግዛት በጀት የተያዘ መሆኑ፣ ድርጅቱ የራሱ እስከሚኖረው ድረስ ግብዓቶችን ለመጫንና ለማውረድ የሦስተኛ ወገንን መሣሪያ በኪራይ አገልግሎት የሚጠቀም መሆኑን ገልጸዋል፡፡

44. እንዲሁም የአርማታ ብረት በኦዲት እና በርክክብ ምክንያት ረዘም ያሉ ወራት ሽያጭ ያልተካሄደ ሲሆን፤ አሁን እየተሸጠ መሆኑና በአጭር ጊዜ ውስጥ ክምችቱ ወደ ገንዘብ የሚለወጥ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

45. የድርጅቱ የስራ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም የኦዲት ቡድን በቃሊቲ መጋዘን በአካል ተገኝቶ ምልከታ ባደረገበት ወቅት በጥጥ መጋዘን ፎሪክሊፍት አለመኖሩ ለማየት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የአርማታ ብረት በርክክብና በኦዲት ምክንያት ለወራት እንዳልተሸጠ ቢገልጹም ነገር ግን ወደ 5 ዓመት ሳይሸጥ በቃሊቲ መጋዘን የተቀመጠ መሆኑ በምልከታ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የስራ ኃላፊዎች በረቂቅ ሪፖርት እና በመውጫ ስብሰባ ላይ በክምችት የነበረው ብረት እንደተሸጠና የተወሰነ ብቻ እናዳለና ቀሪውንም ለመሸጥ በሂደት ላይ እንዳለ ቢገልጹም ነገር ግን ማስረጃው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ አልቀረበም፡፡

46. በመሆኑም ድርጅቱ ግብዓቶች ከጉዳት ተጠብቀው እንዲከማቹ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖችና ተገቢ የመገልገያ መሳሪያዎች እንደ ግብዓቱ ዓይነት ባለመዘጋጀቱ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የግብዓት አቅርቦት ስርዓት እንዳይኖር በማድረግ በደንበኞት ላይ መጉላላትና ቅሬታ የፈጠረ ሲሆን፡ እንዲሁም ንብረቶች በፀሐይ በዝናብና በአቧራ ለብክነት ተዳርገዋል፡፡

ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች ለሚያቀርበው

ግብዓት ዋስትና እንዲያቀርቡ ማድረጉን በተመለከተ፣

47. ድርጅቱ በዱቤ ሽያጭ ግብዓት ለሚረከቡ ኢንዱስትሪዎች ዋስትና እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

48. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ በድርጅቱ ቀርበው በኦዲት ቡድኑ በተከለሱ ማስረጃዎች እንደታየው ድርጅቱ በዱቤ ሽያጭ ግብዓት የሚወስዱ ኢንዱስትሪዎች ለሚረከቡት ግብዓት ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና ወጥነት ባለው መልኩ እንዲያቀርቡ አልተደረገም፡፡ ይህን በተመለከተ የሚከተሉት ጉዳዮች ታይተዋል፡-

- ዲ ኤም ቪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ኢንዱስትሪ ያቀረበው ዋስትና በውስጥ ኦዲት ሲጣራ ያቀረበው ትክክለኛ አለመሆኑ መረጋገጡ፣
- የቆዳ ፋብሪካዎች ከድርጅት ለሚያገኙት የዱቤ ሽያጭ ተመጣጣኝ የባንክ ወይም የኢንሹራንስ ዋስትና እንዲያቀርቡ በወቅቱ ያልተደረገ መሆኑ፣ ሀበሻታኒግ ቆዳ ፋብሪካ ፣ ሆራ ቆዳ ፋብሪካ ፣ ባህርዳር ቆዳ ፋብሪካ አክሰዮን ማህበር ፣ የቃል ኪዳን ሰነደ ከመፈረም ውጭ ዋስትና እንዲያቀርቡ አለመደረጉ፣
- የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ ፣ የባህርዳ ጨርቃ ጨርቅ ለወሰዱት ዱቤ ግዢ ዋስትና ያላቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡
- እንዲሁም የአይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር ጥጥ በግዢ የሚቀርብለት ሲሆን በእነዚህ ጊዜያት ውል ከመፈረም ውጭ ዋስትና አስይዞ የማያውቅ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

49. በድርጅቱ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ድርጅቱ የግብዓት አቅርቦት በጀመረበት ወቅት የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዎች በግብዓት እጥረት ሊዘጉ የደረሰበት ወቅት ነበር፡፡ በመንግስት ለተመረጡት ኢንዱስትሪዎች የቃል ኪዳን ሰነድ በማስፈረም የተመደበላቸውን የተዳመጠ ጥጥ መጠን ውል ፈርመው በዱቤ እንዲገዙ ተደርጓል፡፡

እነዚህ ፋብሪካዎች ኤክስፖርት የሚያደርጉ እና ኤክስፖርት ለሚያደርጉት ግብዓት የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ እነዚህን ኢንዱስትሪዎች መደገፍ ግደታ ነበር፡፡ በሌላ በኩል የተዳመጠ ጥዋ የሚያቀርቡት እርሻዎች ያለዋስትና ቅድሚያ ክፍያ እንዲከፈላቸው ይፈልጉ ነበር፡፡ በወቅቱ ያለው ነባራዊ ሁኔታ የዋስትና አያያዙ ወጥ አለመሆኑና፣ አሁን የማስተካከያ እርምጃም እየተወሰደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

50. በመሆኑም ፋብሪካዎች በዱቤ ሽያጭ ለሚፈጽሙት ግዢ ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና ወይንም ኢንሹራንስ እንዲያቀርቡ ባለመደረጉ የወሰዱትን ዱቤ በወቅቱ እንዳይመለስ ገንዘቡ እንዳይሰበሰብ እንቅፋት ከመሆኑም በላይ የመንግስት እና የህዝብ ገንዘብ በአግባቡ የታሰበው አላማ ላይ እንዳይውል በማድረግ ተጠያቂነት እንዳይጠናከር አድርጓል፡፡፣

ፋብሪካዎች በገቡት ውል የወሰዱትን ብድር እንዲመልሱ ማድረጉን እናበማይመልሱት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረጉን በተመለከተ

51. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ የሚያቀርባቸውን የተለየያዩ ግብዓቶች በገቡት ውል መሰረት በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ ተገቢውን ክትትል ሊያደርግና በወቅቱ በማይመልሱት ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

52. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ በድርጅቱ ቀርበው በኦዲት ቡድኑ በተከለሱ ማስረጃዎች እንደታየው ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ የሚያቀርባቸውን የተለያዩ ግብዓቶች ውል እንዲፈጽሙ እና በገቡት ውል መሰረት በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ ተገቢውን ክትትል በወቅቱ ውጤታማ በሆነ መልኩ አለመደረጉ እንዲሁም በተቀመጠው ጊዜ በማይመልሱት ላይ ተገቢ እርምጃ በወቅቱ የማይወሰድ ሁኔታ መኖሩ ታውቋል፡፡

53. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በታዩ ድርጅቶች ውስጥ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በዱቤ ግዥ ፈጽመው በተቀመጠው ጊዜ/ 6ወር/ ውስጥ ክፍያ ያልፈጸሙ ድርጅቶች እና እስከ (የካቲት 2011 ዓ.ም) ድረስ ያልከፈሉ፣ በድርጅቱም ያልተሰበሰ የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪዎች የሚከተሉት ተቀምጠዋል፡፡፡

- አይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ በዱቤ ከተሸጠ ብር 390,919,000.00 (ሶስት መቶ ዘጠና ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ አስራ

ዘጠኝ ሺ.ህ) ውስጥ ብር 106,568,562.19 አንድ መቶ ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሳ ስምንት ሺ.ህ አምስት መቶ ስልሳ ሁለት ከ19/100 ሳንቲም) የመክፈ.ያ ጊዜው ስድስት ወር ያለፈ ያልተሰበሰበ፣

- ባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አ/ማ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ብር 59,697,000.00 (ሀምሰ ዘጠኝ ሚለዮን ሰድስት መቶ ዘጠና ሰባት ሺ.ህ) ውስጥ ብር 1,220,662.21 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሀያ ሺ.ህ ስድስት መቶ ስልሳ ሁለት ከ21/100 ሳንቲም) የመክፈ.ያ ጊዜው ያለፈ፣
- ካኖሪያ አፍሪካ ጨርቃ ጨርቅ ኃ/የተ/የግ/ማ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ብር 239,503,000(ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን አምስት መቶ ሶስት ሺ.ህ) ውስጥ ብር 36,100,506.29 (ሰላሳ ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ.ህ አምስት መቶ ስድስት ከ19/100 ሳንቲም) መክፈ.ያ ጊዜው ያለፈና በወቅቱ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
- ሐዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በዱቤ ግዢ ከፈጸመው ውስጥ ብር 2,395,261.77 (ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና አምስት ሺ.ህ ሁለት መቶ ስልሳ አንድ ከ77/100 ሳንቲም ያልተሰበሰበ መሆኑ
- እንዲሁም ከቢ.ረ ኢ.ንተርፕራዝ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ውስጥ ብር 101,034,000 (አንድ መቶ አንድ ሚሊዮን ሰላሳ አራት ሺ.ህ) ውስጥ ብር 38,757 ,536.72 (ሰላሳ ስምንት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺ.ህ አምስት መቶ ሰላሳ ስድስት ከ72/100 ሳንቲም) የመክፈ.ያ ጊዜው ያለፈና እስከ የካቲት 2011 ድረስ ያልተሰበሰቡ ናቸው፡፡

54. በተጨማሪም አይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢ.ንቨስትመንት ግሩፕ እ.እ.አ መስከረም 11/2016 በዱቤ ሽያጭ መጠኑ 497,326 ኪ.ግ የሆነ ጥጥ የመሸጫ ዋጋው በብር 35.05 በኪሎ ግራም በአጠቃላይ በብር 17,431,276.30 (አስራ ሰባት ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ አንድ ሺ.ህ ሁለት መቶ ሰባ ስድስት ብር 30/100 ሳንቲም) ተገቢው ውል ሳይፈፀም በዱቤ የተሸጠለት መሆኑ ከተከለሱ ሰነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

55. እንዲሁም በዱቤ ግዥ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ፈጽመው በውል በተቀመጠው ጊዜ / 5 ወር/ ጊዜ እና እስከ የካቲት 2011 ዓ.ም ያልመለሱ የቆዳ ፋብሪካዎች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል፣

- ኢትዮ ሌዘር ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ብር 35,993 ሚሊዮን ውስጥ ብር 3,287,936.76 (ሶስት ሚለዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ ሰባት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ስድስት ከ76/100 ሳንቲም) በወቅቱ ያልተከፈለና የመመለሻ ጊዜው ያለፈ መሆኑ፣
- ሆራ ቆዳ ፋብሪካ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ብር 23,728,069.66 (ሀያ ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሀያ ስምንት ሺህ ስልሳ ዘጠኝ ከ66/100 ሳንቲም) ያልተመለሰ መሆኑ፣
- ሃበሻ ታኒግ በዱቤ ግገር ከፈጸመው ብር 25,411,631.96 (ሃያ አምስት ሚሊዮን አራት መቶ አስራ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ሰላሳ አንድ ከ96/100 ሳንቲም የመክፈያ ጊዜው ያለፈ መሆኑ፣
- ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ በዱቤ ግዥ ከፈጸመው ብር 1,293,859.42 (አንድ ሚሊየን ሁለት መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ ስመንት መቶ ሀምሳ ዘጠኝ ከ42/100 ሳንቲም) ያልተመለሰና ጊዜው ያለፈ መሆኑ፣
- ዴቨ ኢምፔክስ ቆዳ ፋብሪካ በዱቤ ግገር ከፈጸመው ብር 318,330.12 (ሶስት መቶ አስራ ስምንት ሺህ ሶስት መቶ ሰላሳ ከ12/100 ሳንቲም) የመክፈያ ጊዜው ያለፈ መሆኑ፣
- እንዲሁም ይልማ እሸቴ ቆዳና ሌጦ ንግድ ድርጅት በዱቤ ከወሰደው 1,500 ሚሊዮን ውስጥ 791 ሺህ በወቅቱ ያልተመለሰና የመክፈያ ጊዜው ያለፈና በወቅቱ ያልተሰበሰቡ ናቸው፡፡

56. እንዲሁም የአርማታ ብረት በዱቤ ግገር ፈጽመው ያልመለሱ ድርጅቶች ውስጥ

- ዋይ ኤች ኤ የተባለ ድርጅት በዱቤ ሽያጭ በ2008 ዓ.ም ብር 37,341,500 (ሰላሳ ሰባት ሚሊዮን ሶስት መቶ አርባ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር)የወሰደው የአርማታ ብረት ውስጥ ብር 22,160,250 (ሃያ ሁለት ሚሊዮን አንድ መቶ ስልሳ ሺ ሁለት መቶ አምሳ ብር) ብር ያልተከፈለና የመክፈያ ጊዜው ያለፈ መሆኑ፣

- ሃይለ ኪሮስ በዱቤ ሽያጭ ከወሰደው ብር 29,980,500 (ሃያ ዘጠኝ ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሺ አምስት መቶ ብር) ውስጥ ብር 4,180,500 (አራት ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ ሺ አምስት መቶ ብር) የመክፈያ ጊዜ ያለፈ መሆኑ፣
- እንዲሁም ዲ.ኤ.ቪ. ድርጅት በዱቤ ሽያጭ ከወሰደው ብር 52,337,500 (አምሳ ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሺ አምስት መቶ ብር) ውስጥ ምንም ያልተመለሰ እና የጊዜ ገደቡ ያለፈ መሆኑ ከተከለሱ መስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

57. ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ በናሙና የተመረጡ ኢንዱስትሪዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እንደሚከተለው መልሰዋል፡-
    - የአይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፕ የስራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ድርጅቱ ዕዳ ስላለበት ክፍያ ከፍሎ መጨረስ አልቻለም፡፡ ነገር ግን እንደ መፍትሄ የተወሰደው ለውጭ ገበያ ከተመረቱ ምርቶች መሀከል በጥራት ጉድለት ምክንያት ሳይላኩ የቀሩትን ለሀገር ውስጥ ገበያ በማውጣት ከድርጅቱ ጋር በመነጋገር ዕዳ ለመቀነስ የተሞከረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡
    - የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ፋብሪካው ማስፋፊያ ሲያደርግ የነበረ መሆኑ እና የኤክስፖርት ገበያው በመቀዛቀዙ ዕዳቸውን በወቅቱ መክፈል ያልቻሉ መሆኑ፣
    - እንዲሁም ኢትዮ ሌዘር ቆዳ ፋብሪካም በወቅቱ ዕዳቸው ያልከፈሉበት ምክንያት ሲገልጹ በዋናነት የአለም አቀፍ ገበያ በመውረዱ ገበያ ያልነበረ በመሆኑ፣ የዶላር እጥረት ስለነበረ ኬሚካል መግዛት ያልተቻለበትና በወቅቱ ከባንክ ዶላር ለማግኘት እስከ 8 ወር ድረስ የሚያስጠብቃቸው የነበረና ምርት በመያዙ እዳቸውን በወቅቱ መክፈል አለመቻላቸውን፣
    - የሆራ ቆዳ ፋብሪካም የአለም አቀፍ ገበያ በመቀዛቀዙ እዳቸውን በወቅቱ መክፈል ያልቻሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

58. በድርጅቱ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በዱቤ ሽያጭ ከድርጅቱ ፈጽመው እስካሁን ያልመለሱ

ፋብሪካዎች አይካ ኢ.ዲስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንቨስትመንት ግሩፕ አሁን ያለበት እዳ ወለድን ጨምሮ ብር 105 ሚሊዩን የደረሰ ሲሆን ድርጅቱ ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ በብድር የወሰደውን ገንዘብ ስላልመለሰ ባንኩ ተረክቦ እያስተዳደረው የሚገኝ በመሆኑም ባንኩ የድርጅቱን እዳ መዝግቦ እንደከፍል ውይይት የተደረገና ደብዳቤ የተጻፈ መሆኑ ፣ ካኖሪያ አፍሪካ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የመክፈያ ጊዜ ያለፈበትና በአሁኑ ሰዓት ያለበት ውዝፍ እዳ 51 ሚሊዮን ነው ይኽን እዳ በአራት ወራት ውስጥ ከፍሎ ለማጠናቀቅ ስምምነት ላይ የተደረሰ መሆኑ፣ ድሬ ደዋ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ አክሰዮን ማህበር እና አዋሳ ጨርቃ ጨርቅ በፍ/ቤት ውሳኔ አብዛኛው እዳቸውን የከፈሉ መሆኑና ክርክር የሚደረግበት የአዋሳ ጨርቃ ጨርቅ ክፍያም በቅርብ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ የሚያገኝ መሆኑ፣ ከቢረ ጨርቃ ጨርቅ ኢንተርፕራይዝ በአሁኑ ሰዓት ያለበት ዕዳ 38.8 ሚሊዮን ሲሆን በክስ ሂደት ላይ ያለ መሆኑ፤

59. እንዲሁም ሀበሻ ታኒግ ቆዳ ፋብሪካ ውሳኔ በፍርድ ቤት የተወሰነበት ሲሆን ሆራ ቆዳ ፋብሪካ ክስ ላይ ያለ፣ ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ አክሰዮን ማህበር ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑ፣ ኢትዮ ሌዘር ቆዳ ፋብሪካ ዕዳውን ከፍሎ ብር 625,000.00 (ስድስት መቶ ሃያ አምስት ሺ ብር) ዕዳ ያለበት ሲሆን ለድርጅቱ ከሚከፈለው ያለቀለት ቆዳ ግዥ ክፍያ ላይ ተቀንሶ እንዲከፈል ስምምነት ላይ የተደረሰ መሆኑ፣ ይልማ እሸቴ ቆዳ አቅራቢ በፍ/ቤት ክርክር ላይ የሚገኙ መሆኑ፣ እንዲሁም የአርማታ ብረት በተመለከተ ዋይ ኤች.ኤ እና ዲ.ኤም.ቪ በክስ ሂደት ላይ ያለ እና ኃይለ ኪሮስ ፍስሐ ያለበት ቀሪ እዳ ብር13,500.00 መሆኑና ከክስ በፊት ይኽን ቀሪ ገንዘብ ለመሰብሰብ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

60. በመሆኑም ድርጅቱ በዱቤ ሽያጭ የሚያቀርባቸውን ግብዓቶች የሚወስዱ ኢንዱስትሪዎች በገቡት ውል መሰረት በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ ተገቢውን ክትትል ባለመደረጉ እና በወቅቱ በማይመልሱት ላይ እርምጃ ባለመወሰዱ ገንዘቡ ተመልሶ ለሌሎች ግብዓት ለሚፈልጉ እንዱስትሪዎች ተደራሽ እንዳይሆን አድርጓል፡፡ እንዲሁም ድርጅቱ አላማውን እንዳያሳካ በተለያየ ቦታዎች የድርጅቱ መንቀሳቀሻ ገንዘብ እንዲያዝ በማድረግ የገንዘብ እጥረት እንዲከሰት ከማድረጉ በላይ ተጠያቂነት እንዳይጠናከር አድርጓል፡፡

ድርጅቱ ግብዓቶች በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ

ድጋፍ ማድረጉን በተመለከተ

61. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ሊደግፍ ይገባል፡፡

62. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ በድርጅቱ ቀርበው በኦዲት ቡድኑ በተከለሱ ማስረጃዎች እንደተገኘው ድርጅቱ ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ኢንዱስትሪውን በሚፈለገው መልኩ እየደገፈ አይደለም፡፡

63. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በኦዲት ቡድኑ ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው ኢንዱስትሪዎች ለቀረበው ቃለ መጠይቅ እንደሚከተለው መልሰዋል፡፡

- ኤም ኤን ኤስ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪም ድርጅቱ የጥጥ አቅርቦት ላይ እጥረት ያለበት መሆኑን፣
- የባህርዳር ቆዳ ፋብሪካም በቅርብ ከድርጅቱ የገዛው ጨው ብዙ አፈር ያለበትና ጥራት የሌለው እንደሆነ በዚህም ምክንያት ጨው ከደርጅቱ መግዛት ማቆማቸውን እንዲሁም ቆዳን በተመለከተ የተሟላ ባለሙያ የሌለውና ትልቅ የጥራት ችግር ያለበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡
- በተጨማሪም የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካም ድርጅቱ የአቅም ችግር ስላለበት በበቂ ሁኔታ ድጋፍ እያደረገ አለመሆኑን፣
- የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ በ2009 ከድርጅቱ የገዛው ጥጥ በጥራት ጉድለት 20% ብቻ ምርት የሆነ መሆኑንና ነጭ ጥጥ ታዞ ቢጫ ሆኖ የመጣበት ሁኔታ የነበረና ይህም ስራቸው ላይ ትልቅ የገበያ ማጣትን ያስከተለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

64. ጉዳዩን አስመልክቶ በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የስራ ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ድርጅቱ ጥራትን በተመለከተ በቂ ስራ ያልሰራ መሆኑን፣ ይህም ከተቋቋመ አጭር ጊዜ በመሆኑ ምክንያት በተጠናከረ ሁኔታ እየሰራ እንዳልሆነና በፊት ከነበረበት የስራ ባህሪ ተላቅ

በአስተሳሰብ ያልተደራጀ በመሆኑና የኢንዱስትሪው ዘርፍ ጠንካራ አስራር የሚጠይቅ በመሆኑን አሁን ላይ ይህ አቅም እንደሌለው ገልጸዋል፡፡

65. እንዲሁም የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የቆዳ ጥራት ችግር ከእርድ በፊት ወይም በኋላ የሚመጣ ይሆናል፡፡ ድርጅቱ ከዕርድ በኋላ ያለውን ነው የሚከታተል ሲሆን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግዢ ላይ ያሉ ሰራተኞች በስራው ላይ በቂ ዕውቀት ሊኖራቸውና ቆዳው ተገዝቶ ወደ ፋብሪካው እስኪደርስ ድረስ ማቆያ በተገቢ ሁኔታ ሊደረግ እንደሚገባ እንዲሁም ድርጅቱ የምርት ዕወቀት ላይ ክፍተት ያለው ሲሆን በፊት በነረበት አደረጃጀት የሚታሰብ ከሆነ ችግር የሚያመጣና የተፈጥሮ ምርት በመሆኑ ከመበስበሱ በፊት ወደ ምርት ለመውሰድ ስለምርት ማወቅ የሚጠበቅባቸው መሆኑ፣ ነገር ግን እስካሁን ባለው ሁኔታ የዕውቀት ክፍተት መኖሩን ገልጸዋል፡፡

66. በተጨማሪም አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች በተለይ በባህላዊ ሽመና ስራ የተሰማሩ አምራቾች ያለባቸውን ከፍተኛ የግብዓት አቅርቦት ችግር ለመቅረፍ የተደረጉ ጥረቶች ወደ ተጨባጭ ስራ በመግባት ችግሩን ለውጥ ማምጣት በሚያስችል መልኩ መፍታት ያልተቻለ መሆኑ፣ በድርጅቱ የሚገዛ ጥጥ የቃጫ ክር ያለበትና ጥራት ችግር ያለበት መሆኑን ከተከለሱ ዶክመንቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

67. በድርጅቱ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች አማራጭ ገበያ መሆኑና የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ከሌሎች ማግኘት ያልተቻለውን ከድርጅቱ እያገኘ ሲሆን፣ የድርጅቱን የፋይናንስ ምንጭ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ምክንያት ባይጠናከርም በውስን ደረጃ ባለው አቅም የግብዓት አቅርቦት ተግባሩን አጠናክሮ የቀጠለና በ2011 በጀት ዓመት ብር 2.4 ቢሊየን ዋጋ ያለው የተለያዩ ግብዓቶችን ለማቅረብ ያቀደ መሆኑ፡ እንዲሁም የተዳመጠ ጥጥ በመጋዘን የሌለው የጥጥ መሰብሰቢያው ወቅት ባለመሆኑ ሲሆን፤ ጥሬ ቆዳ በከፊል የለፋ (ዌት ብሉ) የሚደረገው የመቆያ እድሜውን ለማራዘም መሆኑና በፈረንሳይ ሽያጭ ቅርንጫፍ በክምችት ያለው ዌት ብሉ ሙሉ በሙሉ የተሸጠ መሆኑ፣ የቆዳ ጥራት የሚጀምረው ከእርባታ ቦታ በመሆኑ ይኸንን ለማሻሻል በሥጋና ወተት ኃብት ኢንስቲትዩት ተገቢው የኤክስቴንሽን ሥራ እየተሰራ እንደሆነና በእርድ ጊዜ እና ከእርድ በኋላ የሚከሰተውን የጥራት መጓደል

ለመከላከል የኢትዮጵያ ቆዳ ልማት ኢንስቲቲዩት ከቆዳ አቅራቢዎች ማህበር ጋር በመቀናጀት እየሰራ በመሆኑ ድርጅቱ አንድም ቆዳ ያለዋጋ እንዳይጣል ማናቸውንም ድጋፍ ለኢንዱስትሪዎቹ የሚያደርግ መሆኑ፣ በሌላ በኩል የዱቤ እዳቸውን ለመክፈል ፍቃደኛ ያልሆኑትን ፋብሪካዎች አይደግፍም፡፡ ድርጅቱ ከኢንዱስትሪዎቹ የሚተርፈውን ጥሬ ቆዳ በመቀበል በከፊል የለፋ/ ሙሉ በሙሉ የለፋ/ ቆዳ አድርጐ በቆዳ ውጤቶች አምራች ኢንተርፕራይዞች ለማቅረብ የኢትዮጵያ ቆዳ ልማት ኢንስቲቲዩት አቅም ለመጠቀም ወይም የሌሎች ፋብሪካዎችን ትርፍ አቅም በመከራየት ለማምረት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

68. በመሆኑም ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በሚፈለጉ መልኩ ድረጋፍ ባለመደረጉ ኢንዱስትሪዎች ጥራት ያለው ምርት በማምረት በአለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ እንቅፋት ይፈጥራል፡፡እንዲሁም ሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ዋጋ የከፈለችለት(የተለያዩ ድጋፎች የተደረጉለት ዘርፎች) እና ያቀደችውን የውጭ ምንዛሬ በማሳጣት በሀገሩቱ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ አስተዋፅኦ አሳድሯል፡፡

2. ድርጅቱ ኢንዱስትሪዎች በመደገፍ ውጤታማ እንዲሆኑ የምርት ግብዓት አቅርቦት ሰንሰለት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

ድርጅቱ የገበያ ትስስር ሰንሰለት በመዘርጋ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ፣

69. ድርጅቱ ቀልጣፋና ውጤታማ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የአቅርቦት ሰንሰለት ማኔጅመንት ሊተገብር ይገባል፡፡

70. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ በድርጅቱ ቀርበው በኦዲት ቡድኑ በተከለሱ ማስረጃዎች ድርጅቱ የኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ በማቋቋሚያ ደንቡ ላይ የተገለጸ ቢሆንም ነገር ግን

ድርጅቱ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የሆነ የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦት ሰንሰለት በመዘርጋ ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ አለመደረጉ ታወቋል፡፡

71. በድርጅቱ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የግብዓት አቅርቦት ሰንሰለቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ጅምር ሥራዎች መኖራቸው ሆኖም መጠናቀር እንዳለበት በመግለጽ የጥጥ የኮንትራት እርሻ ከጥረት ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር ሥራ ላይ ለማዋል እቅድ ተይዞ እየተሰራ የሚገኝና የቆዳ እና የቆዳ ውጤቶች የእሴት ሰንሰለት ጥናት እየተካሄደ መሆኑና በጥናቱ ውጤቱ መሠረት ወደ ሥራ ለመግባት የታቀደ መሆኑ ነገር ግን አንዳንድ ባለሀብቶች ለዘላቂ ጥቅም በጋራ ከመስራት ይልቅ በአጭር ጊዜ ጥቅም በሚያስገኙ ነገሮች ላይ የሚያተኩሩ በመሆኑ ይህ ለድርጅቱ ፈተና እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

72. በመሆኑም የአቅርቦት ሰንሰለት ማነጅመንት ስርዓት ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ባለመደረጉ በየዘርፉ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ጥራታቸውን ጠብቀው ለሚፈለገው አላማ በወቅቱ እንዳይውሉ አድርጓል፡፡

ድርጅቱ የብድር አሰጣጥ ውል በጥናት የተደገፈ መሆኑን በተመለከተ፣

73. ድርጅቱ ከፋብሪካዎች ጋር የግብዓት የአቅርቦት ውል ከመፈጸሙ በፊት የፋብሪካዎቹ የቀደመ የፋይናንስ አቋም እና እዳ አከፋፈል ተገቢውን ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡

74. ይሁን እንጂ ጉዳዩን አስመልክቶ በድርጅቱ ቀርበው በኦዲት ቡድኑ በተከለሱ ማስረጃዎች እንደታየው ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ ግብዓት በሚያቀርብበት ጊዜ ዱቤ ከመስጠቱ በፊት የፋብሪካዎቹን አቋምና የዕዳ አከፋፈል በተመለከተ ተገቢውን ጥናት ሳያደርግ የዱቤ ሽያጭ የሚያደርግበት ሁኔታ መኖሩ፣ ለማሳያ ያህል በናሙና ከታዩ ፋብሪካዎች መሀከል የኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ ድርጅቱ የፋብሪካዎችን የመክፈል አቅም ጥናት ሳይደረግ ብድር የተሰጠ መሆኑታወቋል፡፡

75. በድርጅቱ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ድርጅቱ የግብዓት አቅርቦት በጀመረበት ወቅት የግብዓት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ኢንዱስትሪዎች በኢንስቲቲዮቶች ተለይተው እና

ተመርጠው የተሰጡትን የመለየት ችግር የነበረበት ሲሆን አሁን ባለው ሁኔታ የዱቤ ሽያጭ የሚጠይቅ ተቋም በተገቢው ሁኔታ ማጣሪያ ሳይደረግ አገልግሎትን እንዲያገኝ የማይደረግና ለነባር ደንበኞች ተጨማሪ የዱቤ አገልግሎት ከመስጠት በፊት የቆየ የዱቤ እዳ አከፋፈላቸው በተገቢው ሁኔታ የሚታይ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

76. በመሆኑም የቀደመ የፋይናንስ አቋም እና እዳ አከፋፈል ተገቢውን ጥናት የማይደረግበት ሁኔታ በመኖሩ ኢንዱስትሪዎች በዱቤ የሚወስዱትን ግብዓት የዱቤ ክፍያውን በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ተመላሽ እንዳይሆንና ለሚፈለገው ዓላማ እንዳይውል አድርጓል፡፡

ድርጅቱ ውጤታማ ለሆኑ አቅራቢዎች የሚያበረታታ መሆኑ በተመለከተ፣

77. ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በማቅረብ ውጤታማ ለሆኑ አቅራቢዎች ማበረታቻ የሚሰጥበትን ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

78. ይሁን እንጂ ድርጅቱ ኢንዱስትሪዎች ውጤታማና ቀጣይነት ያለው ግብዓት እንዲያገኙ ግብዓቶችን በማቅረብ ውጤታማ የሆኑ አቅራቢዎች ለማበረታት የሚያስችል ማበረታቻ የሚሰጥበት ስርዓት የሌለው መሆኑ፣

79. በድርጅቱ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ማበረታቻ የምንለው ቅድሚያ አገልግሎት መስጠትን ነው፡፡ አንዳንዴ በተወሰነው የጊዜ ገደብ እዳቸውን መክፈል ሲያቅታቸው ለጥቂት ጊዜ ማራዘምና መታገስ እንዲሁመ የአገልግሎት ቅድሚያ እንዲያገኙ ማድረግ ነው ማበረታቻ የምንለው፡፡ በሌላው አለም ግን ምርታቸው ሳይሸጥ ከቀረ ገበያ የማዘጋጀት ድረስ ይሄዳል በእኛ አሰራር ግን እዳቸውን የማይከፍሉ አብረውን እንዳይሰሩ ስናደርግ የሚከፍሉትን ችግራቸውን የተወሰነ በመታገስ አብረውን እንዲሰሩ እናበረታታለን፡፡

80. የድርጅቱ የሥራ ኃላፊ ይህን ቢሉም አቅራቢ ድርጅቶች ጋር በዘላቂነት አብሮ ሊያሰራ የሚያስችል ተገቢ የማበረታቻ ስርዓት በጥናት በማስደገፍ ያልሰሩ በመሆኑ እና ለማበራታት ሰራን ያሉትም በግብአት አቅራቢዎች ላይ ተፈላጊውን ውጤት ስለማስገኘቱ ማስረጃውን ባለማቅረባቸው ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡

81. በመሆኑም ለኢንዱስትሪዎችና ለአምራቾች አስፈላጊ የሆነ ማበረታቻ የሚሰጥበት ስርዓት ባለመኖሩ አምራች ኢንዱስርሪዎችና አቅራቢዎች ምርታቸውን በተሻለ ሁኔታ እንዳያቀርቡ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ክፍል ሦስት

የመደምደሚያ ሀሳቦች

82. የኢንዱስትሪ ግብዓቶች አቅርቦት ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን በድርጅቱ የተደረጉ ጥረቶች መኖራቸውን እንረዳለን፤ ከክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በመንግስት የሚወጡ አዋጆች እና ደንቦች እንዲሁም በመ/ቤቶች የተዘረጉ የአሰራር ስርዓቶች እና የወጡ መመሪያዎች በአግባቡ ተፈፃሚና ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ አንፃር ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች አቅርቦት ስርዓት አፈጻጸም ውጤታማነት በኦዲቱ በሚገመገምበት ወቅት ከዚህ በታች የተመለከቱ ዋና ዋና የአሠራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡

- የግብዓት አቅርቦት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድርጅቶችን መገንባት ማስተዳደር እንዲሁም አሰፈላጊ ሲሆን ማስተላለፍ፣ እንዳለበት በመቋቋሚያ ደንቡ 328/2006 የተቀመጠ ቢሆንም ነገር ግን በድርጅቱ ይህን በተመለከተ የተሰራ ስራ አለመኖሩ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በማምረት ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ማቅረብ ያለበት ቢሆንም ስራው አለመሰራቱ ታውቋል፡፡

- ድርጅቱ በማቋቋሚያ ደንቡ 328/2006 የኢንዲስትሪ ግብዓቶችን ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር በመግዛት የሚያቀርብ ቢሆንም ኢንዱስትሪውን ሊደግፍ በሚችል መልኩ ግብዓቶችን ከአገር ውስጥ እና ከውጭ በግዢ ውጤታማ በሆነ መልኩ እያቀረበ አለመሆኑ ታውቋል፡፡

- ድርጅቱ የሚመራበት የረጅም ጊዜና የአጭር ጊዜ አቅጣጫ አመለካች እስትራቴጂክ/ ዕቅድ የሌለው መሆኑ፣ እንዲሁም ድርጅቱ በየዘርፉ ለኢንዱስትሪዎች የሚያቀርባቸው ግብዓቶችን በዓይነትና በብዛት በመለየት እስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት በዚያው መሰረት አመታዊ ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ ያልተደረገና በአፈጻጸም ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች ተገቢው እርምጃ የማይወሰደበት ሁኔታ መኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ድርጅቱ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖች በማዘጋጀት እንደ ግብዓቱ ዓይነት በመለየት አስፈላጊ የሆኑ መገልገያ መሳሪያዎችና የመጋዘን መርጃ መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያልተደራጀ መሆኑ ታውቋል፡፡

- ❖ በዱቤ ሽያጭ ግብዓት የሚወስዱ ኢንዱስትሪዎች ለሚረከቡት ግብዓት ተመጣጣኝ የሆነ ዋስት ወጥ በሆነ መልኩ እንዲያቀርቡ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡
- ❖ ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ የሚያቀርባቸውን የተለያዩ ግብዓቶች ውል እንዲፈጽሙ እና በገቡት ውል መሰረት በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ ተገቢውን ክትትል በወቅቱ ያላደረገና በተቀመጠው ጊዜ በማይመልሱት ላይ ተገቢው እርምጃ በወቅቱ ያልወሰደ መሆኑ፣
- ❖ ድርጅቱ ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ኢንዱስትሪውን በሚፈለገው መልኩ እየደገፈ አለመሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ❖ ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችል ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ
- ❖ ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ ግብዓት በሚያቀርብበት ጊዜ ዱቤ ከመስጠቱ በፊት የፋብሪካዎቹን አቋምና የዕዳ አከፋፈል በተመለከተ ተገቢውን ጥናት ሳያደርግ የዱቤ ሽያጭ የሚያደርግበት ሁኔታ መኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ❖ ድርጅቱ ኢንዱስትሪዎች ውጤታማና ቀጣይነት ያለው ግብዓት እንዲያገኙ ግብዓቶችን በማቅረብ ውጤታማ የሆኑ አቅራቢዎች ለማበረታት የሚያስችል ማበረታቻ የሚሰጥበት ስርዓት የለውም፡፡

83. የኢንዱስትሪ ግብዓቶች አቅርቦት ስርዓት ተዘርግቶ ውጤታማና ቀልጣፋ ሆኖ በሚፈለገው መልኩ እንዳልተከናወነ ያሳያል፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ በሚቀጥለው የሪፖርት ክፍል በኦዲቱ ወቅት የታዩትን የአሰራር ክፍተቶች ለማሻሻል አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ተብሎ የታመንባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች

- ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓት አቅርቦቶችን ለማረጋገጥ የኢንዱስትሪውን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል ጥናት በማጥናት ችግሮችን በመለየት እና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ቅደም ተከተል (Priority) ጥናት በማድረግ ድርጅቶችን ሊገነባ እና ግብዓቶችን በአገር ውስጥና በውጭ አገር በማምረት ሊያቀርብ ይገባል፡፡
- ድርጅቱ ኢንዱስትሪዎች ጥራት ያለው ምርት በማምረት ውጤታማና ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ ግብዓቶችን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር የገበያ ጥናት በማድረግ ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ በመግዛት ሊያቀርብ ይገባል፡፡
- ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በዓይነትና በብዛት በመለየት እስትራቴጂክ ዕቅድ ሊኖረውና ያን መሰረት ዓመታዊ ዕቅዱ በማዘጋጀት በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርግ እና በአፈጻጸም ላይ የሚታዩ ክፍተቶች በመለየት ተገቢውን የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ከጉዳት ከብክነት ሊጠበቁና ሊከማቹ የሚችሉባቸው ደረጃቸውን የጠበቁ አስፈላጊ የሆኑ መጋዘኖችና የመጋዘን የመገልገያ መሳሪያዎች እንደ ግብዓቶቹ ዓይነት ሊደራጅ ይገባል፡፡
- ድርጅቱ በዱቤ ሽያጭ ለሚያቀርባቸው ግብዓቶች ኢንዱስትሪዎቹ ለሚረከቡት ግብዓት ተገቢ ዋስትና እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ የሚወስዱት ገንዘብ ለታለመለት አላማ እንዲውል ግብዓት ሲያቀርብ በገቡት ውል መሰረት በተቀመጠው ጊዜ እንዲመልሱ ተገቢውን ክትትል ሊያደርግና አስፈላጊው እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ድርጅቱ ኢንዱስትሪዎች ጥራት ያላቸው ምርቶች በማምረት ለገበያ እንዲያቀርቡና ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ የሚያስፈልጋቸውን ግብዓቶችን በጥራት፣ በተመጣጣኝ ዋጋና በጊዜ በማቅረብ ኢንዱስትሪዎቹን በተሻለ ሁኔታ ሊደግፍ ይገባል፡፡

- ድርጅቱ ኢንዱስትሪዎች በሀገር አቀፍና በአለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ምርታማነታቸው እንዲጨምር ቀጣይነት ያለው ጠንካራ የአቅርቦት ሰንሰለት ማኔጅመንት ሊተገብር ይገባል፡፡
- ድርጅቱ አምራቾች/ኢንዱስትሪዎች ከድርጅቱ ግብአቶችን በዱቤ ሽያጭ ለማግኘት ጥያቄ ሲያቀርቡ አገልግሎቱን ከመስጠቱ በፊት የፋብሪካዎቹን የቀደመ የፋይናንስ አቋምና ዕዳ አከፋፈል ተገቢውን ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በማቅረብ ውጤታማ ለሆኑ አቅራቢዎች ተነሳሽነታቸው እንደጨምር ማበረታቻ የሚሰጥበት ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

አባሪ 1 መመዘኛ መስፈርት

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit issue)	የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria)
1. ድርጅቱ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎችን በምርት ጥራት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እና እንዲጎለ ብቱ እንዲሁም ሀገሪቱ በዘርፉ የምታገኘውን ገቢ ለማሳደግ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የግብዓት አቅ ርቦት ስርዓት መዘር ጋቱንና ተግባራዊ መደ ረጉን መገምገም፣ 1.1የኢንዱስትሪዎች ምርታማነትና ውጤታማነትን ለማሳደግ ለኢንዱስትሪ የሚያ ስፈልጉ ግብዓቶችን በጥራት፣ በብዛት እና በጊዜ ለኢንዱስ ትሪዎች የሚቀርብበት የአሰራር ስርዓት የዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም፣	1. ድርጅቱ የግብዓት አቅርቦቶችን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ድርጅቶችን በመገንባት፣ በማስተዳደር እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡
	2. ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በመግዛት ሊያቀርብ ይገባል፡፡
	3. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በዓይነት፣ በጥራት እና በብዛት በመለየት በእስትራቴጂክ ዕቅዱና በዓመታዊ ዕቅዱ ሊያካትትና በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	4. ድርጅቱ በኢንዱስትሪ ግብዓቶች አቅርቦት አፈጻጸም ዕቅድ ክንውን ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች በመለየት የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
	5. ድርጅቱ ግብዓቶች ከጉዳት ተጠብቀው እንዲከማቹ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖችና ተገቢ የመገልገያ መሳሪያዎች እንደ ግብዓቱ ዓይነት ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡
	6. ድርጅቱ በዱቤ ሽያጭ ግብዓት ለሚረከቡ ኢንዱስትሪዎች ዋስትና እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit issue)	የመመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria)
	7. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች በዱቤ ሽያጭ የሚያቀርባቸውን የተለየያዩ ግብዓቶች በገቡት ውል መሰረት በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እንዲመልሱ ተገቢውን ክትትል ሊያደርግና በወቅቱ በማይመልሱት ላይ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
1.2 ድርጅቱ ኢንዱስትሪዎች በመደገፍ ውጤታማ እንዲሆኑ የምርት ግብዓት አቅርቦት ሰንሰለት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፣	8. ድርጅቱ ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ኢንዱስትሪዎችን ሊደግፍ ይገባል፡፡
	9. ድርጅቱ ቀልጣፋና ውጤታማ የኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የአቅርቦት ሰንሰለት ማኔጅመንት ሊተገብር ይገባል፡፡
	10. ድርጅቱ ከፋብሪካዎች ጋር የግብዓት የአቅርቦት ውል ከመፈጸሙ በፊት የፋብሪካዎቹ የቀደመ የፋይናንስ አቋም እና እዳ አከፋፈል ተገቢውን ጥናት ሊያደርግ ይገባል፡፡
	11. ድርጅቱ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን በማቅረብ ውጤታማ ለሆኑ አቅራቢዎች ማበረታቻ የሚሰጥበትን ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡